# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ ፡፡ገበሬ፡፡ነጋዴ፡ወታደር፡፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

ቁጥር 2 ቀን 21/12/66


## የየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴና የሰራተኛው ሚና

ስራ የሃብት ምንጭ ነው፡፡ስራ ያለሰራተኛ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ሰራተኛ የሃብት የብልጽግና መሰረትና ፈጣሪ ነው፡፡ የህብረተሰብ ምሰሶና አውታር፡ደገፍና ገትር፡ ቀጥ አድርጐ የሚይዘው ሰራተኛ ነው፡፡ በጠቅላላው ሰርቶአደር ስንል በፋብሪካ በንግድ በግብርና በከብት እርባታና በሌሎችም ተግባሮች ላይ የተሰማራ፡በቀጥታም ሆነ በዘወርዋራ መንገድ ለሰው ልጅ ህይወት ተፈላጊ የሆኑትን ነገሮችና አገልግሎቶች የሚያበረክት ወይም በእንደዚህ አይነት ተግባር የሚሳተፍ ማለትን ያሰማል፡፡ ስለሆነም እዚህ ሰርቶአደር ወይም ሰራተኛ ስንል ጠበብ ባለ ትርጉም፡ በፋብሪካ በንግድና በሌሎችም ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ውስጥ በመቀጠር ጉልበታቸውን ወይም እውቀታቸውን እየሸጡ የሚኖሩ ማለታችን ነው፡፡

ሰራተኛ በጉልበቱና በአእምሮው ሃይል ሃብት ይፈጥራል፡፡ ከሚፈጥረው ሃብት ግን የሚደርሰው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከበርቴዎች አብዛኛውን እጅ ይወስዱበታል፡፡ በዚህ ምክንያት ከፍተኛ ብዝበዛና ምዝበራ፡ጭቆናና ግፍ ይሰራበታል፡፡ በመደብ በተከፋፈለና የመንግስቱን ስልጣን ባላባቶችና ከበርቴዎች በያዙበት ህብረተሰብ ውስጥ ሰራተኛው የወዙን ፍሬ እየተበዘበዘ ከመኖር ሌላ ምንም አይነት ምርጫ እንደሌለው ታሪክ በጉልህ ይመሰክራል፡፡ ከዚህ አሰቃቂ ሁኔታ ራሱን ነፃ ለማውጣት የሚችለው በቁራጥነትና ባንድነት በመታገል ብቻ እንደሆነም ታሪክ ያስተምረናል፡፡

በኢትዮጵያስ የሰርቶአደሩ ሁኔታ እንዴት ነው. ይህ ነው የማይባል ብዝበዛ፡ጭቆና፡ግፍ አለበት፤ ህይወቱ ምድራዊ ሲኦል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የኢምፔሪያሊስቶች ቡችላ የሆነው አድሃሪው መንግስት ሰራተኛውን በሄራዊና ባእዳን ከበርቴዎች እንደእቃ እንዲጠቀሙበት አሳልፍ ሰጥቶአቸዋል፡፡ አሰሪው ሰራተኛውን በፈለገው ደመወዝ ይቀጥረዋል፤ እንደአሰኘው ከስራ ያባርረዋል፡፡ ሰራተኛው ምንም አይነት ዋስትና የለውም፤ የስራው ሁኔታ እንዲሻሻልለት፡የድካሙን ዋጋ እንዲያገኝ አሰሪውን ከመለማመጥ በስተቀር ሌላ ነገር ለማድረግ አይፈቀድለትም፤ ጭንቅ ሲሆንበት፡ሲበዛበት፡ሲያንገፈግፈው፡የመጨረሻ መሳሪያው የሆነውን የስራ ማቆም መብቱን ሊጠቀምበት በሚነሳበት ጊዜ የከበርቴዎች ጥቅም ጠባቂ የሆነው ቡችላ መንግስት በመጨቆኛና በመደምሰሻ ሃይሉቹ/በፖሊስና በወታደር/ ያስጨፈጭፈዋል፤ ደሙን እንደከረምት ጐርፍ ለማፍሰስ አይመለስም፡፡ የከበርቴዎቹ ብዝበዛና ዘረፋ፡የአድሃሪው መንግስት ግፍ በደል ጭቆና እጅግ በጣም የበዛ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ አልፎ ይሄዳል፡፡ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ከአለም ሰራተኞች ውስጥ የባሰ የተጉሳቆለ፡የተመዘበረ፡የብዝበዛው ከብደት ያጉበጠው ፡የመጨረሻው ጭቁን መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ሰራተኛ ከዚህ ከባርነት ራሱን ነፃ ለማውጣት ከባድ ትግል ሲያደርግ ቆይቶአል፡፡ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አሻንጉሊቶች ፀረሰራተኛ ሕግ በማውጣት ሰራተኛውን እጅና እግሩን ጠፍረው ለከበርቴዎች ከመስጠታቸው በፊት የፈረንሳይና ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ሰራተኞች፡

የሲሚንቶ ፋብሪካ ሰራተኞች፡ የጥጥ ፋብሪካ ሰራተኞች ማህበር አቋቁመው የጭቆናውንና የብዝበዛውን ቀንበር ለመስበር ከባድ ትግል ሲያካሂዱ እንደነበረ የሚታወስ ነው። በሕግ ስገርብረት ቢታሰርም ሰራተኛው መፍጨርጨሩን፡መታገሉን አላቆመም፣ ከሰፊው ሕዝብ በተለይ ከተማሪው ጋር በመደጋገፍ የመደብ ጠላቶን ለመቋቋም ትግሉን ሲያካሂድ ቆይቶ ታሪካዊው የየካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ፈነዳ።

የየካቲቱ እሳተገሞራ ከመፈንዳቱና አገሪቱን ከማጥለቅለቁ በፊት በ1965 መጨረሻ ገደማ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰራተኞች፡በዚህ አመት/በ1966/ የወንጂና መተሃራ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች፡ የመልካ ሴዴ የአርሻ ተክል ሰራተኞችና ሌሎችም ከባድና ቀራጥ ንቅናቄ በማድረግ፡ህይወታቸውን ጭምር በመሰዋት፡በአሰሪያቸና በቡችላው መንግስት ላይ ድልን መቀዳጀታቸው የታወቀ ነው። በየፋብሪካውና በየድርጅቱ ደረጃ የሰራተኛው ትግል እየተጠናከረና እየተፋፋመ ሲሄድ ታሪካዊው የካቲት ዱብ አለ።

በሌላ በኩል፡በከፍተኛ ደረጃ ላይ የኢትዮጵያን ሰራተኞች በማጠቃለል የመሪነቱን ቦታ የያዘው ኢሰአማ በሰራተኛው ትግል እንቅስቃሴ ውስጥ ምን ስፍራ ነበረው? በየካቲቱስ የሰፊው ሕዝብ ታሪካዊ መነሳሳት ምን ነበረ አቋሙ? ሰፊው ሰርቶአደር በሚገባ አሰለፍታል ወይ?

የኢትዮጵያ ሰራተኞች አንድነት ማህበር የሰርቶአደሩን አንድነት ለማጠንከር፡መብቱንና ጥቅሙን ለመጠበቅ ሳይሆን፡ለብዝበዛ ለዘረፋ ለጭቆና እንዲመቻቸው ለማድረግ ኢምፔሪያሊስቶች በተለይ አሜሪካኖች የፈጠሩት የከበርቴዎች መሳሪያ ነው። ላይ ላዩን አንድነት ይላል፣ ውስጥ ውስጡን ይከፋፍላል። በአፉ የሰራተኛን መብት አስከብራለሁ፡ጥቅሙን አስጠብቃለሁ በማለት ያውጃል፣ በእርግጥ ግን የሚያደርገው የዚህን ተቃራኒ ነው። የአድሃሪው ፊውደቡርዧ ጥገኛ መንግስትና የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ ቡችላ በመሆን የኢትዮጵያን ሰርቶአደር ያስበዘብዛል፡ያስጨቁናል፡ያስደበድባል፡ያስበድላል፡የግፍ ግፍ ያሰራርታል።

የኢሰአማ መሪዎች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የቡችላው አድሃሪ መንግስት ፍጡሮች ናቸው እንጂ ከሰራተኛው ውስጥ የወጡ የሰርቶአደሩ ወኪሎች አይደሉም። የሰራተኛውን አንድነትና ንቅናቄ ለማዳከምና ለመስበር በልዩ ልዩ አይነት የተንኮል ዘዴ ይጠቀማሉ። በጥቅምና በመላሸ፡በሹመት መደለል ማባበል፡በነገድ በጐሳ በሃይማኖት መከፋፈል፣ ማስፈራራት መወንጀል ማስከሰስ ማስገልበጥ ከስራ ማስወጣት ማስደብደብ ማስገደል፣ በእነዚህና በመሳሰሉት ርካሽና እርኩስ ድርጊቶች በመጠቀም የሰራተኛውን የትግል ንቅናቄ ለመግታትና ለማዳከም በሙሉ ሃይላቸው እንደሚጥሩ የታወቀ ነው። የተሸጡት የኢሰአማ መሪዎች ይህንን ወንጀለኛ የአሰራር ዘዴ የወረሱት ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች መሆኑን በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል።

በየነ ሰሎሞን ለአስራአንድ አመታት ቀንዳም የአሜሪካን ቡችላ በመሆን በኢሰአማ ላይ ነግሶአል። ከተሳሳኪነትና ከተራ ሰራተኛነት ተነስቶ በመለማመጥ፡ጫማ በመላስ፡ጭራ በመቁላት፡ ነገር በመስራት፡ለሲአይኤና ለፀጥታ መስሪያ ቤት ወሬ በማቀበል፡በሰራተኛው ላይ በመሰለል፡ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ንቅናቄ ወደፊት እንዳይራመድ አፍኖ ይዞታል። ለእግሩ እንኳን ጫማ ያልነበረው ምስኪን ዛሬ ትልቅ ዲታ ሆኖአል። ቪላው በሁለት ሶስት ይቆጠራል፣ ዚታዎቹም እንደዚሁ፣ ንግዱ እርሻው፡ስንቱ ተቆጥሮ. እንደነድርጅ ሚኒ እንደነጃምስ ሆፋ /ባለሚልዮን ብር አሜሪካውያን 'የሰራተኛ መሪዎች'/ ለመሆን ምንም ያህል አልቀረውም። ለምሳሌ ያህል ነው እንጂ በየነ ብቻውን አይደለም። እነፍስሃጽዮንም ከሲአይኤ የሚያገኙት ገንዘብ ጉጉታቸውንና ስግብግብነታቸውን ስለአጋለባቸው ከሃብታሞች በመጋባት ከፍተኛ ስልጣንና ሃብት ለመጨበጥ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው። ሌሎቹም እንደዚሁ ናቸው። ነገሩ 'ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ' ነው።

ታጋዩንና ቆራጡን የኢትዮጵያ ሰርቶአደር ንቅናቄ ወደፊት እንዳይራመድ እንቅፋትና መሰናክል የሆኑት እነዚህ አይሁዳዎች፡በየካቲቱም ታሪካዊ የሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴ ሰራተኛው ተገቢ ቦታውን እንዳይዝ ትልቅ ጥረት አድርገዋል። ከስር ሰራተኛው ፈንቅሎአቸው ባይነሳ ኖሮ የአራቱም

ቀናት ጠቅላላ ስራ ማቆም አይደረግም ነበር:: /እንዳለካቸውን በመደገፍ ፍስሃጽዮን የስራ ማቆሙን ውሳኔ ተቃውሞት ነበር:: በተጨማሪም ሰራተኛው ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርግ የኢሰአማ አድርባዮች አወናብደውታል::/ ከዚያም ወዲህ ሰራተኛው እነርሱን ወደዚያ ጥሎ ትግሉን በራሱ እንደቀጠለ ነው:: በተንኮላቸው እያጨናገፉትና እያወናበዱት ንቅናቄውን መልክ እንዳይዝ:ቀጥታ ወደጠቅላላና ብሄራዊ ጉዳይ እንዳይተላለፍ:ከሰፊው ሕዝብ ጋር እንዳይሰለፍ:የትግሉን መሪነት እንዳይወስድ:ታሪካዊ ስፍራውን እንዳይዝ ከባድ እክል መሆናቸውን አስመስክረዋል:: ሰራተኛው እነዚህን እስስቶች የሚያስወግድበት ጊዜው ሩቅ መሆን የለበትም:: የሰራተኛው ንቅናቄ ደንበኛውን አግጣጫ ሊይዝ የሚችለውና ትግሉም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊካሄድ የሚችለው እነዚህን ተንኮለኞች አድርባዮች በቅድሚያ ሲያባርር ብቻ ነው:: አሁን በቅድሚያ ሰርቶአደሩ ሁሉ እነዚህን የሲአይኤ መሳሪያዎች ድራሻቸውን ማጥፋት ይኖርበታል::

ኢሰአማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት:የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም:የሲአይኤ ምሽግ መሆኑ መቅረት አለበት:: ኢሰአማ የኢትዮጵያን ወዝአደር መብት አስከባሪና ጥቅም ጠባቂ:የኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ አደራጅና መሪ መሆን አለበት:: ወደፊት ተራማጅ እንጅ ወደሃላ ተመልካች የፊውደቡርዧው አድሃሪ መንግስትና የበላይ ጠባቂው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የስለላና የፀረሕዝብ ወንጀሎቹ መፈፀሚያ:የሲአይኤ አፋኝ ጋድ:ማፊያ መሆን የለበትም::

እዚህ ላይ ግልጥ መሆን ያስፈልጋል:: ለኢምፔሪያሊዝምና ለአድሃሪው መንግስት የተሸጡትን ደላሎችና ሰላዮች ማውገዛችንና ማጋለጣችን ነው እንጅ የኢትዮጵያን ሰራተኞች አንድነት:ኢሰአማን መቃወማችን አይደለም:: ይህ ያለአንዳች ጥርጣሬ በግልጥ መታወቅ አለበት:: ኢሰአማን የሚመሩ: ከሰራተኛው ወገን የሆኑ:ሌሎች ሃቀኞችና ትጉሆች ለሰራተኛውና ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስቡ:የሚቆረቆሩ ችሎታ ያላቸው መሪዎች መሆን አለባቸው:: ሰርቶአደሩ እንደዚህ አይነት መሪዎች አሁን ቶሎ ብሎ ይምረጥና ታሪካዊ ሚናውን ይያዝ ነው የምንለው:: ልዩነቱን ደህና አድርጎ መገንዘብ ያሻል::

ኢሰአማ ቶሎ ብሎ እነዚህን ወደሃላ ጎታች የሲአይኤ ቡችሎች ያባርር ስንል:በየካቲት ፈንድቶ በመገንፈል ላይ ባለው የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢና ታሪካዊ ስፍራውን እንዲይዝ በማለት ነው:: ይህ ታሪካዊ ስፍራው ምንድነው? የትግሉን አላማ /አይዲዮሎጂ/ መግለጽና ማብራራት:የሰፊውን ሕዝብ ትግል በደንብ ማደራጀት፣ድሃውና መሬትአልባ የሆነ ጭሰኛ ገበሬ /ከጠቅላላው ሕዝብ 80% ገደማ የሚሆነው/ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚደረገውን ትግል በደንብ እንዲደግፍና ከሰራተኛው ጋር አብሮ እንዲሰለፍ አስፈላጊውን ማድረግ፣ ዝቅተኛው ነጋዴ:ጠቢቡና ባለእጁ:ሰራአጡ:በድርብ በዝበዛና ጭቆና ስር የሚማቀቁት ብሄረሰቦች:ወታደሩና ምሁሩ ወዘተ. በሰራተኛው የትግል ባንዲራ ስር እንዲሰለፉ ማድረግ የኢሰአማ አቢይ ተግባር ነው:: ይህ ነው የኢሰአማ ታሪካዊ ሚና::

የኢሰአማ /ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሰራተኞች/ ዋና ጊዜያዊ ተግባር ምን መሆን አለበት?

1. ኢሰአማን ፀረሰራተኛ ከሆኑት ከአሁኖቹ መሪዎችና ከአደገኛው የአሜሪካን የስለላ ድርጅት ማጽዳትና ነፃ ማውጣት፣ ለሰራተኛው መብትና ጥቅም በሃቅና በትጋት የሚሰሩ መሪዎች ከሰራተኛው መካከል በአስቸኳይ መምረጥ፣
2. በአሁኑ መሪዎች ደንታቢስነትና ከሃዲነት ከስራ የተባረሩት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰራተኞች ቶሎ በለው ወደስራቸው እንዲመለሱ:ማናቸውም ሰራተኛ ከስራ እንዳይወገድ: የኑሮ ዋጋ ማስተካከያ ደመወዝና ሌሎችም መንግስት በገባው ቃል መሰረት እንዲፈፀሙ አጥብቆ መታገል፣
3. በመካሄድ ላይ ያለውን የሰፊውን ሕዝብ እንቅስቃሴ መልክ መስጠት:ማቀናበር:ማደራጀትና መምራት፣ በእንቅስቃሴው ውስጥ የበለጠ እንዲሳተፍ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፣

4. በሰርቶአደሩ አይዲዮሎጅ ስር ከተሰለፉት ግንባር ቀደም ምሁራን ጋር ባንድነት በመተባበር፡ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ትግል የሚያደራጅ፡ የሚያቀናብርና የሚመራ አንድ አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋም፣
5. የሰፊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በቀርብ እንዲመሰረት፡ እስከዚያው ድረስ አሁኑኑ ከሰፊው ሕዝብ የተውጣጣ ጊዜያዊ መንግስት እንዲቋቋም፡ ካሁኑ ጀምሮ መሰረታዊ ሰባዊና ብሄራዊ መብቶችና ነፃነቶች አስፈላጊው ዋስትና ተሰጥቶ ስራ ላይ እንዲውሉ እንዲደረግ አጥብቆ መታገል::

እውነተኛው ኢሰአማ ለዘላለም ይኑር፣
የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፡ ሲአይኤና ቡችሎቹ ይውደሙ፣
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::

## ታሪክን የሚገነባው ሰፊው ሕዝብ ነው::

በአሁኑ ያረጀ የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ/ባላባታዊ/ ስርአተማህበር ውስጥ እንደሰፊው ሕዝብ ክፍሎች የሚቆጠሩት የሰራተኛው መደብ፡ ጪሰኛውና ድሃ ገበሬው፡ ትናንሽና መለስተኛ ነጋዴዎች፡ ዝቅተኛና መለስተኛ የመንግስት ሰራተኞች፡ ተራ ወታደርና መለስተኛ መኮንኖች፡ ተማሪዎችና አብዛኛው ምሁራን፡ ሾፌሮችና ታክሲ ነጅዎች፡ ጠቢቦች፡ ሰራአጦችና....ወዘተ.ና ቸው::

የሕብረተሰቡን ጠቅላላ ህይወትና እድገት የሚወስነው የሰፊው ሕዝብ የርባታ ተግባርት ነው:: ሰፊው ሕዝብ ለህብረተሰቡ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ቀሳቁሶች ሰርቶ ከማውጣቱም ሌላ የስራ መሳሪያዎችን ያሻሽላል፣ ከስራ ልምምድ የሚቀስመውን እውቀት እያከማቸ ከትውልድ ወደትውልድ በማስተላለፍ በርባታ ትግበርቱ አንድ ስርአተማህበርን ወደሌላ ከፍተኛ ስርአተማህበር ለማራመድ አስፈላጊ የሆነውን ማቴሪያላዊ/ቁስአካላዊ/ መሰረት ይገነባል:: በዚህ አድራጐቱ ነው እውነተኛውን የሰው ልጅ ታሪክ የሚገነባው::

ሰፊው ሕዝብ ራሱን ከበዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሚያወጣው ራሳቸውን 'ዝቅ' በማድረግ 'ለተራው ሕዝብ' ደግ ለመዋል በሚሞክሩ ታላላቅ ሰዎች ብርታት ሳይሆን በራሱ ትግል ነው:: ይህን እውነት በቲዎሪ ማወቅ ምናልባት በጣም አስቸጋሪ ላይሆን ይችላል:: በተግባር ላይ ማዋሉ ግን ይህን ያህል ቀላል ሆኖ አልተገኘም:: ከታሪክ እንደምንረዳው ከዚህ በፊት ብዙ የፖለቲካ ቡድኖች ሪቮሉሲዮናዊ አላማዎችን ይዘው ስርአተማህበሩን ለመለወጥ ታግለው፣ ግባቸውና ሚናቸው ተከከለኛ ሆኖ እያለ ሰፊው ሕዝብ የታሪክ አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑን በመዘንጋታቸው ራሳቸውን እንደነፃአውጭዎች በመቁጠር የሰፊውን ሕዝብ ሪቮሉሲዮናዊ ችሎታ በመናቅ፡ ሱታፌውን ስላላረጋገጡ ብቻ በበዝባዥ መደቦች ተደምስሰው ሊጠፉ በቅተዋል::

ዛሬ ባገራችን ካለፈው የካቲት ጀምሮ በሚደረገው የመሰረታዊ ለውጥ እንቅስቃሴ 'ኢትዮጵያ ትቀደም' የሚለውን አላማ ይዞ በግንባር ቀደምነት የሚገኘው የጦር ሃይሎች ደርግ ወደዚህ አይነት ከባድ የታሪክ ስህተት እንዳይወድቅ ያሰጋል::

ጠቅላላው ሰራዊት የሕዝቡን ፈቃድ እንዲፈጽም በዲሞክራሲያዊ መንገድ መርጦ ያቋቋመው አስተባባሪ ደርግ ሰፊውን ሕዝብ በመፍራት ወይንም በመናቅ ይሁን አይታወቅም ከወታደሩ የተወከለበትን ተግባር በሚገባ ለመፈፀም ካለመብቃቱም ሌላ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ጥርጣሬንና ቅሬታን እስከማተረፍ ደርሶአል::

'ኢትዮጵያ ትቀደም' በማለት በሰራዊቱ በተጀመረውና በሕዝቡ በተደገፈው ንቅናቄ ሰፊው ሕዝብ እንዲሳተፍ ደርጉ ምንም መንገድ አልከፈተም:: እንዲያውም የሰፊውን ሕዝብ ሱታፌ ለመቀነስ የጽሁፍና የንግግር ነፃነት እስካሁን ድረስ እንደታገደ እንዲቆይ ከማድረጉም በላይ ሰፊው ሕዝብ

እንዳይሰበሰብ ሰጥብቅ ከልከሎአል:: በአንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶችም የሰራተኞችን ኰሚቴዎች እንዲፈርሱ አድርጉአል:: ከዚህም አልፎ ተርፎ በሰፊው ሕዝብ ላይ ደጋግሞ ዘቶአል:: ራሱን እንደነፃአውጭ ግንባር በመቁጠር 'እኛ ከሌለን የአገሪተዋ ደህንነት የለም' ሲል ፊውዳላዊ የሆነ አስተሳሰብ ሰንዝሮአል::

ደርጉ እንደዚህ አይነቶቹን ድርጊቶች ሲፈጽም ምናልባት እንደገዥው መደብ ፈላስፎች ሰፊው ሕዝብ ደደብ ደንቆሮ መንጋ ነው ብሎ ይገምት ይሆን ? ወይንስ ሰፊውን ሕዝብ ፈርቶ ነው? ይህ ከሆነ ሰፊው ሕዝብ ከመሳፍንት የበለጠ አስፈርቶት ይሆን በንቅናቄው ውስጥ መሳፍንት እየተቀያየሩ ሲሳተፉ ሕዝቡ ቆሞ ብሎ ብቻ እንዲመለከት የሚያስገድደው! እንግዲያውማ ደርጉ የማን ወገን ነው! የሰፊው ሕዝብ ወይስ የመሳፍንትና የመኳንንት!

ሰፊው ሕዝብ በንቅናቄው መሳተፍ አለበት፤ መብቱና ግዴታው ነው:: በስሙ የሚሰራውንና ሊሰራ የታቀደውን ሁሉ ማወቅ መብቱም ግዴታውም ነው:: ስለዚህ ከደርጉ ጥርት ያለ ዝርዝር የሥራና የአላማ ፕሮግራም ይጠይቃል:: 'ኢትዮጵያ ተቅደም' የሚለው መርህ ያለዝርዝር ፕሮግራም ግልጽ ፍች ሊኖረው አይችልም:: ስለዚህ ሰፊው ሕዝብ ያለዝርዝር ፕሮግራም በንቅናቄው ሊሳተፍም ሆነ ያለጥርጣሬ ሙሉ ድጋፉን ሊሰጥ አይችልም:: ለመሆኑ ደርጉ ዝርዝር የሥራና የአላማ ፕሮግራም ለሕዝቡ እንዲያስታውቅ ደጋግሞ ሲጠየቅ ለሕዝቡ ጥያቄ የዝሆን ጆሮ የሚሰጠው ለምን ይሆን! የፕሮግራም ማውጣቱ ስራ ይህን ያህል ከባድ ሆኖ ነው ወይንስ ከሰፊው ሕዝብ ሊደበቅ የተፈለገ ነገር ቢኖር ነው?

የዝርዝር ፕሮግራም መፍፍና የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ የሚደግፉ እንደነሻለቃ ተፈራ ተክለአብ ያሉ ተራማጆች በደርጉ ውስጥ መኖራቸው ታውቋል:: ነገር ግን የሰፊውን ሕዝብ ወገን በመውሰዳቸው ብቻ ደርጉ አንዳንዴ ሲያስራቸው አንዳንዴም ፈትቶ በጥብቅ ሲከታተላቸው መታየቱ በደርጉ ላይ ትልቅ ጥርጣሬን አስከትሎአል:: እንዲሁም በአርሚ አቬሽን፡በጦር ሃይሎች የህክምና ክፍልና በጦር ሃይሎች የመሃንዲስ ክፍል ላይ ጭቆና የደረሰባቸው ዝርዝር ፕሮግራም ወጥቶ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ እንዲሳተፍ በመጠየቃቸው ብቻ መሆኑ በጣም የሚያስገርም ነው:: ሰፊው ወታደር ደርጉን የወከለው ለእንደዚህ አይነቱ ተግባር አልነበረም::

አሁንም ሰፊው ወታደር በደርጉ ውስጥ በሚታዩት ጉድለቶች ላይ ውይይት ካደረገ በሗላ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በፍጥነት አንድ መፍትሄ ካላገኘለትና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል ወደፊት እንዲራመድ ለማድረግ ካልበቃ በሌሎች አገሮች ከዚህ በፊት እንደተደረገው ሕዝቡ በወታደሩ ተስፋ ቆርጦ የራሱን ጦር ሃይል ለመገንባት ከመገደድ ሌላ ምን ምርጫ ይኖረዋል! ይህስ አይቻልም ተብሎ ይጠረጠር ይሆን?

በሌላ በኩል ደግሞ ክቡር ደርጉን በትህትናና በሃቀ የምናሳስበው እንደዚህ አይነት ትችት ሲቀርብ የግል ጥቅምን ለመሻት ወይንም ሕዝቡን ሲጨቁኑና ሲበዘብዙ ኑረው አሁን የታሰሩትን የመንግስት ባለስልጣኖች ለመርዳት አይደለም:: ደርጉን በጥሞና ለማስገንዘብ የምንወደው ከጠላት በሚሰነዘረው አፍራሽ ሂስና ከሕዝብ ወገን በሚሰነዘረው ገንቢ ሂስ መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ እንዲረዳልን ነው:: ከዚህ በፊት በዚሁ ጋዜጣችን እንዳመለከትነው ሁሉ ደርጉ የሕዝቡን ፍላጐት የሚያረኩ አንዳንድ ድርጊቶችን በመፈፀሙ ድጋፍ ሊያገኝ ይገባዋል:: ደግሞም በሃላፊነት ቦታ ሲገኙ ስህተት ከፈፀሙ ያለምንም ፍርሃት በገንቢ ሂስ መታረም፤ ወይንም ስህተት ሲደረግ ካዩ ማመልከት ግዴታ ነው:: ከዚህ በላይ በደርጉ ላይ የቀረቡትም ሂሶች በዚህ አውደ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ እንጅ ደርጉን በሃሰትና በተንኮል ለማጥላላትና ለማውደም በመፈለግ አይደለም:: ደርጉ ጥፋት ሲያደርግ በገንቢ ሂስ ማረም፤ አድሃሪ ሃይሎች በደርጉ ላይ ቢነሱ በጉኑ በመሰለፍ መታገል፤ ይህ ነው የማንኛውም አውነተኛ ተራማጅ የሕዝብ ወገን አቋም::

ወደዋናው ጉዳይ እንመለስና፤ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ የግድ መሳተፍ አለበት:: 'ኢትዮጵያ ተቅደም' የሚለው መርህ ያለዝርዝር ፕሮግራም ፍች ሊኖረው አይችልም፤ ያለሰፊው ሕዝብ ሱታፌም

ዘለቄታ ሊኖረው አይችልም:: በከባድ አማርኛ የተፃፉ ብዙ ጽሁፎችን ደጋግሞ ከማሰማት ይልቅ ቀጥታ ገንቢና ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል:: ልጅ ወልደማርያምን በልጅ ገብረማርያም መለወጥ ለይስሙላ ያህል ከሕዝብ ወገን መጡ የሚባሉ አንዳንድ ሰዎችን መሾም ብቻ ለትግሉ መመሪያ የሚያስፈልገውን ዝርዝር ፕሮግራምና ለዘለቄታው ዋስትና የሆነውን የሰፊው ሕዝብ ሉዓላዊ ሊተኩ አይችሉም::

ለምሳሌ ትላንት የተወሰደው እርምጃ —አጤ ሃይለስላሴ ንብረቴ ነው በማለት የሚያናፉበት ቤተመንግስት የሕዝብ መደረጉ:አጤ እንዴት አድርገው የሕዝብን ሃብት ለባለሟሎቻቸው በመርጨት እንደሚያባክኑ ለሕዝብ መገለጡ— ደርጉን በሕዝብ ዘንድ የሚያስወድደውና ሙሉ ድጋፍ የሚያስጠው ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አልፎ አልፎ ብቅ የሚል ነጠላ ድርጊት ግልፅና ሃቀኛ የሆነን ጠቅላላና ዝርዝር ፕሮግራም ለሕዝብ መግለፅ አስፈላጊነቱና አስቸኳይነት ከቶ አይቀንሰውም::

አሁን፣ሕዝቡ ከደርጉ ከሚጠባበቃቸውና ደርጉም በአስቸኳይ መውሰድ ከሚገባው እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይገባል:—

1. የልጆች መንግስት ወደዚያ ተወግደ ከወታደርና ከሲቪል የተውጣጣ የተራማጆች ጊዜያዊ መንግስት ዉሉ ሳያድር እንዲቋቋም፣
2. የዚህን ጊዜያዊ መንግስት መቋቋም ለማፋጠን ሰፊው ሕዝብ በትግሉ እንዲባተፍ ካሁኑ ያለምንም የጊዜ ገደብ የንግግር:የጽሁፍ:የመሰብሰብና የፖሊቲካ ማህበርር የማቋቋ ነፃነት በስራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ፣
3. የመሬት ይዞታ ጣራ ዝቀ ተደርጉ ተወስና መሬት ለጪሰኞች እንዲደለደል፣
4. አሰሪዎች ሰራተኛውን ከስራ ማባረራቸው እንዲከለከል፣ ከስራ የተባረሩ እንደበላቴ አርሻ ሰራተኞች ያሉት በአስቸኳይ ወደስራቸው እንዲመለሱ ትእዛዝ እንዲተላለፍ፣ ከአሁን ጀምሮ ምንም አይነት ስራ እንዳይዘጋ፣ በቀርብ የተዘጉትንም የስራ ቦታዎች /ፋብሪካዎች ወዘተ./ በሙሉ በሰራተኛውና በመንግስቱ ትብብር እንዲካሄዱ እንደገና መከፈት፣ የኑሮ ዋጋ ማስተካከያ የደመወዝ ጭማሪ እስካሁን ሳልተደረገላቸው ሰራተኞች እንዲደረግ፣
5. የድርቅ ቀበሌዎችን ችግር ለማቃለል:
   ሀ/ ካገርና ከውጭ አገር እርዳታ በሰፊው እንዲጠየቅ፣ እንዲሁም ከመንግስቱ ልዩ ባጀት እንዲመደብላቸው፣
   ለ/ ታማኝና ችሎታ ያላቸው ሰዎች የእርዳታውን ማከፋፈል ስራ እንዲያከናውኑ፣ አሁን የሚደረገው የእርዳታውን ገንዘብ ማባከን ጉዳይ ቶሎ እንዲወገድና በአጥፊዎቹ ላይ ከባድ እርምጃ እንዲወሰድ፣
   ሐ/ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ቀደም ብለው ባቀረቡት ሃሳብ መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ ፕሮግራም ታውጆ:ት/ቤቶች ተዘግተው ተማሪዎች ለተወሰነ ጊዜ በድርቅ ቀበሌዎች የእርዳታ ማከፋፈልንና የልማት ተግባሮችን እንዲያከናውኑ፣
6. እስካሁን ያልተፈቱ የፖለቲካ እስረኞች በፍጥነት እንዲፈቱ፣
7. እያሌ ያልታሰሩ የሕዝብ ጠላቶች አሁንም ተንደላቅቀው ግፍ በመፈፀም ላይ ስለሚገኙ በሙሉ እንዲታሰሩ፣በተለይም የፊውዳሉ ስርአት ቁንጮ በመሆናቸው ሕዝቡን የበደሉና ያስበደሉ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለተፈፀመው ግፍ ሁሉ ዋና ተጠያቂ የሆኑት አጤ ሃይለስላሴና ንጉሳዊ ቤተሰብ ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ከሕዝብ ላይ በግፍ የተሰበሰበው የንጉሳዊ ቤተሰብ ሃብት በሙሉ በመንግስት እንዲወረስ፣
8. ሙሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና ነፃነቶችን የሚሰጥና የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል የሚችል ሕገመንግስት በቶሎ ታውጆ ስራ ላይ እንዲውል፣

እነዚህና መሰሎቻቸው እርምጃዎች አጣዳፊነታቸው ታውቆ በስራ ላይ ባይውሉ ደርጉ ከትልቅ ሃላፊነት ላይ መውደቁን በጥብቅ እንዲያስብበት ያስፈልጋል::

ከሰፊው ሕዝብ ጋር ወደፊት እንራመድ::